የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No. 44
ADDIS ABABA, 31th July, 2026

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፱/፪ሺ፲፰

ለዘላቂ እና ሁሉን አቀፍ የእድገት ልማት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ…………..…...........…ገጽ ፲፱ሺ፰፻፹

**Content**

Proclamation No. 1429/2026

International Development Association Loan Agreement for Inclusive Growth Development Policy Financing Ratification Proclamation...............................Page 19880

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፱/፪ሺ፲፰

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ዘላቂ እና ሁሉን አቀፍ የእድገት ልማት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የሚውል ፬፻፴፯ ሚሊዮን ፬፻ሺ (አራት መቶ ሰላሳ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሺ) ኤስዲአር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፰ዓ.ም የተፈረመ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION No. 1429/2026

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** the Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association stipulating that International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to 437,400,000 (Four Hundred Thirty-Seven Million Four Hundred Thousand) Special Drawing Rights, for Inclusive Growth Development Policy Financing was signed on the 25th day of June 2026;

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም ባካሄደው ፩ኛ ልዩ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለዘላቂ እና ሁሉን አቀፍ የእድገት ልማት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፱/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 8084 -ET በዚህ አዋጅ ጸድቋል።

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፬፻፴፯ ሚሊዮን ፬፻ሺ (አራት መቶ ሰላሳ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሺ) ኤስዲአር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**WHEREAS**, the House of Peoples Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified this agreement at its 1st special session held on 26th day of June, 2026;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for Inclusive Growth Development Policy Financing Ratification Proclamation No. 1429/2026".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Credit Number 8084- ET signed on the 25th day of June 2026 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to 437,400,000 (Four Hundred Thirty-Seven Million Four Hundred Thousand) Special Drawing Rights, in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force upon its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 31st day of July, 2026**

**TAYE ATSKESELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**